# <u>የምሁራን ደናቁርት ፫</u>

በዚሁ ኣርእስት ባለፉት ኣከታትለን ያወጣናቸው ጽሑፎችን በመቀጠል ለማስረጃ የሚሆኑን ሁለት ታሪካዊ ሰዎችን እናቀርባለን። ከነዚህም ኣንደኛቸው ከሓዲ፣ ሌላው ደግሞ እውነተኛ ሀገር ወዳድና ሓቀኛ ኢትዮጵያዊ ጀግና የሆኑት ናቸው።

በመጀመሪያ የጠቀስናቸውን የነጋድራስ ኣፈወርቅ ገ/ኢየሱስን ጉዳይ በዙ ሰው ታሪኩን ባለማወቁና እንዲዘረዘርም ስለ ጠየቀን፣ ከዚህ ቀጥለን ባጭሩ እንገልጸዋለን። ነጋድራስ ኣፈወርቅ ከሀገራችን ቀደምት ምሁራን ሲሆኑ በምኒልክ ዘመን በጣልያን ኣገር በቋንቋ ኣስተማሪነት በመሰማራታቸው "ፕሮፌሶር" ተብለዋል። ልዑል ራስ መኰነን የውጫሌን ውል ሊፈራረሙ ጣልያን ኣገር በሄዱ ጊዜ ነጋድራሱ በኣስተርጓሚነት ቆመው፣ ውሉን በማወቅ ይሁን በስሕተት፣ ተጣምሞና የሚያሳስት ሆኖ እንዲቀርብ ኣደረጉት ተብለው ይታማሉ። ያ ግን ከሓዲ ኣላሰኛቸውም። ጅራትና ጉድ ከኋላ እንዲሉ ጉዱ ገና ነው።

በውሉ መጣመም ምክንያት በጣልያንና በኢትዮጵያ ጦርነት ሲነሳ በኤውሮጳ የነበሩት ነጋድራስ ኣፈወርቅ ሮጠው እጃቸውን ለጣልያን ሰጡ። ከጀኔራል ባራቴሪ ተልከውም በኣሥመራ፣ እናት ሃገራቸውን በመካድ በፖለቲካ ሥራና በኣስተርጓሚነት ሲያገለግሉ ቆዩ። ጣልያን በዓድዋ ጦርነት ሲሸነፍም ወደ ኢጣልያን ኣገር ሸሽተው ተመልሰዋል።

ይህ ከሓዲነታችው የመጀመሪያው ሲሆን በዚያ ኣላበቃም። ሃፄ ኃይለሥላሴ ምሕረት ኣድርገውላቸው፣ 'በኢጣልያን ሃገር ምሁርና ኢትዮጵያዊ ፕሮፌሰር ኣሉልን' ተብሎ፣ በሮማ ከተማ የኢትዮጵያ ኣታሼ እንዲሆኑ ተሾሙ። በኢጣልያን ወረራ ዘመን ደግሞ ለሁተኛ ጊዜ ለጠላት ባንዳነት ገብተው፣ የክሕደት ክሕደታቸው በኣሥመራ ከተማ ለነበረው የባዕድ ራድዮ ጣብያ ኣንባቢ በመሆን፣ "ጣልያን እኛ ሓበሻን ለማስተማርና ልታሰለጥነን፣ <u>*ለተቀደሰ ዓላማ*</u> እንጂ በሌላ ክፋት ኣልመጣችም..." እያሉ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የጠላት ፕሮፓጋንዳ ማስተጋብያ ሆኑ። ዳግመኛው ክሕደታቸውም እሱ ነበር።

በኣምስቱ ዓመት የወረራ ዘመንም ነጋድራስ ኣፈወርቅ ገብረኢየሱስ በኣዲስ ኣበባ ኣፈ-ቄሳር በመባል ከፍተኛ ባለስልጣን ሆነው፣ ከግራሲያኒ ጐን ኣይይለዩም ነበር። ጀግኖቹ ኢትዮጵያውያን ኣብርሃ ደቦጭና ሞገስ ኣስገዶም በየካቲት ዓስራሁለት ቀን በግራሲያኒ ላይ ቦምብ ጥለው ሲያቆሰሉት፣ ነጋድራሱ ግራሲያኒን ከመሬት ኣንስተው፣ ታቅፈውት በኣምቡላንስ፣ ዛሬ 'ራስ ደስታ' ወደሚባል ሆስፒታል ከወሰዱት ሰዎች ኣንዱ ናቸው።

የነጋድራስ ኣፈ-ቄሳር ገብረኢየሱስ ፍጻሜ ግን ኣላማረም፤ ኃፄ ኃይለሥላሴ ከስደት ሲመለሱ ተይዘው፣ በከሓዲነት ተከስሰው፣ ለፍርድ ቀረቡ። ታድያ የዘመኑ የምሁራን ደናቁርትን "ከሓዲያን" የምንላቸው እንዲሁ ያለ ምክንያት ሳይሆን፥ የሕግ ጠበቆችና ኣዋቂዎች፣ የሕግም ኣርቃቂዎች ስለሆኑ፣ ሕጋዊ-ትቅድምት (legal precedence) የሚባለውን ያውቃሉና፣ ይህን የሃገራችን ታሪክን ተመርኲዘን ነው።ይህንን ማስረጃ ኣይተውም ከክሓዲነታቸው ይታረማሉ፣ ይመለሳሉ ብለንም ተስፋ እናደርጋለን።

ነጋድራስ ኣፈ-ቄሳር በቀረበባቸው የክሕደት ክስ ሞት ሲፈረድባቸው፣ ሃፄ ኃይለሥላሴ ግን በምሕረት ወደ 'ዕድሜ ይፍታሕ' ግዞት ለወጡላቸው። በጅማ ከተማ ኣካባቢም ከሰማንያ ዓመት ዕድሜ በላይ ኖረው፣ ዓይናቸውን ታውረው፣ ኣርጅተው መሞታቸው ይነገራል። ***'የምሁራን ደናቁርት'*** ላልናቸው ለጥቂቶች የዘመኑ ቡድን የመጀመሪያ መሪ እኚህ ከሓዲ ፕሮፌሰር ሲሆኑ፣ ዛሬም በዱካቸው የሚከተሉ ስናይ በጣም እናዝናለን።



ከሓዲው ፕሮፌሰር (ነጋድራስ ኣፈወርቅ ገ/ኢየሱስ ኣፈ-ቄሳር) በሮማ የኢትዮጵያ ኣታሼ ሆነው በነበሩበት ጊዜ ከኢጣልያንዋ ሚስታቸው ጋር የተነሱት ፎቶግራፍ።

በሚቀጥለውና የመጨረሻው ጽሑፋችንም ምንም የዘመናዊ ትምህርት ባይኖራቸውም፣ ታላቅ ኢትዮጵያዊ ሃገር ወዳድ የነበሩ፣ ግሩምና ጀግና የሆኑ ሰው ይዘን እንቀርባለን።

ገ/ኢ. ጐርፉ።